ተዛማጅ ግብአቶች: ACA, COA, COA-RA, IGN, IGO-RA, IHC-RA, IJA-RA, IOE-RA, IOE-RB, IOI-RA, IOH-RA

ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት: Deputy Superintendent; Office of School Support and Well-being; Office of District Operations

# ማህበራዊ-ስሜት እና የአእምሮ ጤና
# የተማሪዎች ፕሮግራሚንግ እና አገልግሎቶች

## A. ዓላማ

ለተማሪዎች ማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነት እና የአእምሮ ጤና አስፈላጊ የትምህርት እና የአካዳሚክ ስኬት አካል በመሆኑ፣ የትምህርት ቤት ክትትል እና ትምህርት ማጠናቀቅ የትምህርት ቦርድ ያለውን ቁርጠኝነት ማረጋገጥ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ ተልእኮ የሚደግፉ ሁለገብ፣ ትኩረትን እና የተጠናከረ የተማሪ አገልግሎቶች ስርዓትን ለመዘርጋት።

## B. ጉዳዩ

የተማሪዎች ትምህርት እና የአካዳሚክ ስኬት፣ በትምህርት ቤት መገኘት እና ትምህርትን ማጠናቀቅ ሁሉም የጠንካራ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አእምሯዊ ጤንነት አካል ናቸው፡ የመማርና የግንዛቤ ፍላጎቶች፣ በትምህርት ቤት ሕጎች፣ ደንቦች፣ እና የሚጠበቁ ስርአቶች መሠረት ለመምራት የማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አእምሯዊ ጤንነት ፍላጎቶች እና አካላዊ ፍላጎቶች በትምህርት ቀን ንቁ ሆነው እንዲሳተፉ። የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ተማሪዎች በአካል በትምህርት ቤት ህይወት ውስጥ ሲሳተፉ ጤናማ እና የራሳቸውን ደህንነት እንዲሁም የሌሎችን ደህንነት የሚጠብቁ እና የሚያበረታቱ አወንታዊ ውሳኔዎችን እያደረጉ እንዲያድጉ ያበለጽጓቸዋል።

## C. አቋም

1. ቦርዱ የተማሪዎችን አካዴሚያዊ ስኬት በበርካታ የተለያዩ እርከኖች ለመደገፍ ይፈልጋል

    a) በተገቢ የመግባቢያ ሠነዶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ባለሙያዎችን ችሎታ እና ሪሶርሶች እንዲሁም የማህበረሰብ ኤጋር ኤጀንሲዎችን በአግባቡ ይጠቀማል፣ እና

b) በፖሊሲ COA መሠረት፣ የተማሪዎች ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም እና "Be Well 365" ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት ድባብ ማስፈን ከሚደግፉ ተነሳሽነት ካላቸው ጋር ያጣጥማል።

2. ባለብዙ ደረጃ ያለው የመማር ስርዓት የሚከተሉትን ቁልፍ የትምህርት ተግባሮችን ማካተት አለበት ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፡

a) ለሁሉም ተማሪዎች ዩኒቨርሳል ፕሮግራሚንግ – ክፍል ደረጃ-ተኮር እና ከእድሜ ጋር የሚመጥን ትምህርት በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) ሥርዓተ-ትምህርት ስለ ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት፣ የጤና ትምህርት እና የአእምሮ ጤና ሊተርሲ፣ጉልበተኝነትን መከላከል የመሳሰሉ ትምህርት ቤት አቀፍ ፕሮግራሞች፣ እና ከትምህርት ቤት የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች የድጋፍ አገልግሎቶች።

b) የታለሙ የተማሪ ድጋፎች - በትምህርት ቤት ደረጃ የተማሪ ደህንነት ቡድኖች (SWBT) እና የትምህርት አስተዳደር ቡድኖች (EMTs) ልዩ የተማሪ ፍላጎቶችን እና ጥንካሬዎችን ከግምት ውስጥ ለማስገባት እና የባህሪ ድጋፍ እና ጣልቃገብነቶችን ለማዳበር በአጭር ጊዜ በግለሰብ እና በቡድን ካውንስሊንግ አማካይነት ስጋቶችን ለይቶ ማወቅ፣ ወደ ማህበረሰብ አጋሮች ማስተላለፍ፣ የአነስተኛ ቡድን ክህሎቶች ስልጠና፣ እና የተናጠል ጉዳይ አያያዝ።

c) የተጠናከረ ድጋፍ – ለግለሰብ ወይም የቡድን ቴራፒ/ሕክምና ወደ ማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች ማስተላለፍ፣ ከትምህርት ለሚቀሩት የቤት ውስጥ ጉብኝቶች/ጣልቃ-ገብነት፣ የባህሪ ስጋት ግምገማ፣ ራስን የማጥፋት ዝንባሌ ግምገማ፣ እና ያጋጠመ ቀውስ ካለ ጣልቃ በመግባት መታደግ።

d) ሁሉንም ሪሶርሶች የሚገመግሙ እና ባለሙያዎችን የሚያደራጁ የት/ቤት ካውንስለሮችን፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስቶችን፣ የት/ቤት ማህበራዊ ሰራተኞችን (SSWs) እና ቀጥተኛ አገልግሎት ሰጭ ባለሙያዎችን፤ የተማሪ ሰራተኞች (PPWs)፣ ታዳጊ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ቴራፒዩቲካል ካውንስለሮች (ETCs)፣ እና የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች (PCC) በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ጠንካራ እና ደጋፊ የአመራር ቡድኖች።

3. ቦርዱ በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች እና የታመኑ ጎልማሶች አስፈላጊነት ከማህበራዊ-ስሜታዊ እና የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች በተጨማሪ በየቀኑ ከተማሪዎች ጋር መስተጋብር የሚፈጥሩ፣ በጭንቀት፣ በጭንቀት ወይም በችግር ጊዜ ለተማሪዎች ርኅራኄን የሚያሳዩ እና ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የሚተማመኑባቸው እና ተንከባካቢ የድጋፍ ምንጭ አድርገው ሊመለከቷቸው እንደሚችሉ ያረጋግጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች እና እንደአግባቡ ከተማሪዎች ጋር በመደበኛነት

የሚገኙ በነ ፈቃደኞች ስለተማሪዎች የአእምሮ ጤና ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እውቀት እንዲኖራቸው፣ ስለትምህርት ቤት SWBTs እና EMTs ተግባራት እና ማህበራዊ-ስሜታዊ እና ወቅታዊ ግንኙነቶችን በሚመለከት MCPS የመማር አላማዎችን እና የድጋፍ መርጃዎችን ያዘጋጃል።

4. ከፖሊሲABC ጋር የተገናዘበ፣ የቤተሰብና-ትምህርት ቤት ትብብር የትምህርት ቦርድ የተማሪ እና ቤተሰብ የማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነት እና የአእምሮ ጤና ድጋፎችን፣ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን በቀጥታ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ወይም በማህበረሰብ አጋሮች አማካይነት ያበረታታል።

a) ተማሪዎች በት/ቤት ከሚገኙ የ MCPS ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አእምሯዊ ጤና ባለሙያዎች ጋር በመደበኛነት በአካል የመገናኘት እድሎች ይኖራቸዋል፣ እነርሱም የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት SWBT ጨምሮ በአግባቡ ለተማሪዎች ያለውን ፕሮግራም እና አገልግሎቶች እንዲገነዘቡ ይረዷቸዋል።

b) MCPS በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ስለሚገኙ የማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነት አገልግሎቶች፣ የአእምሮ ጤና ባለሙያዎችና ፕሮግራሞች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች አማካይነት ወይም በማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች በኩል ለቤተሰቦች እና ለተማሪዎች የማሳወቁን ተግባር ገቢራዊ ያደርጋል።

5. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ሚስጥራዊ የተማሪ መረጃን ይፋ የማድረግ ፍቃድ በፌዴራል የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች የጤና መረጃ ማስተላለፍን በተመለከተ ለተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ተገዢ ሊሆኑ ይችላሉ።

5.6. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከማህበረሰብ አጋር ኤጀንሲዎች ጋር የትብብር ሚናዎችን እና ሃላፊነቶችን፣የሪፈራል ሂደቶችን፣የደህንነት እቅድ ማዘጋጀትን፣የውሳኔ አሰጣጥ ህጎችን እና ሚስጥራዊነትን እና የውሂብ ማጋራት ፕሮቶኮሎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን እና ፕሮግራሞችን ከሚመራው FERPA እና የጤና አገልግሎት የሚሰጡትን ከሚቆጣጠረው HIPAA ጋር በሚጣጣም መልኩ እንደአግባቡ የመግባቢያ ሠነዶችን ይመሰርታል።

## D. ተፈላጊ ውጤቶች

1. ሁሉም ተማሪዎች ጤናማ፣ጠንካራ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ እና ስኬታማ ወጣቶች በመሆን ያድጋሉ፥ በትምህርት ላይ የተሰማሩ እና የራሳቸውን እና የሌሎችን ደህንነት የሚጠብቁ እና የሚያበረታቱ አወንታዊ ውሳኔዎችን ያደርጋሉ።

2. ተማሪዎች የማህበራዊ-ስሜታዊ እና የአእምሮ ጤና ፕሮግራሞችን ዓላማዎች ለመረዳት ሲፈልጉ እንደአስፈላጊነቱ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ተደራሽነት ይኖራቸዋል።

፳3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ ተልእኮ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁለንተናዊ፣ ዒላማ ያደረገ እና የተጠናከረ የተማሪ አገልግሎቶች ሥርዓት በመዘርጋት ለውጤታማ ትምህርት አስፈላጊ የሆኑትን አወንታዊና አክብሮት የተሞላበት አውድ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን በማዳበር ይደገፋል።

E. የአተገባበር ስልቶች

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፡-

1. ተማሪዎች ለዕድገታቸው ደረጃ የሚመጥን የማህበራዊ-ስሜታዊ እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ የሚያግዙ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ፣ የማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት እና የጤና ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርትን መተግበር፤

2. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ግብዓቶች እና/ወይም ከማህበረሰብ አጋሮች የሚሰጠውን እያንዳንዱን ማህበራዊ-ስሜታዊ እና አእምሯዊ ጤና ፕሮግራም በብቃት ተደራሽ ለማድረግ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች በትምህርት ቤት ደረጃ ርዕሰ-ተኮር መረጃ መስጠት፤

3. ስለ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና የአእምሮ ጤና ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ተደራሽነት ከባለድርሻ አካላት መደበኛ ግብረመልስ መሰብሰብ፣ እና

4. በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተዘረዘሩትን የትኩረት አቅጣጫዎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ ሂደቶችን ማቋቋም፣ እና በፖሊሲ COA፣ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም በተገለጸው መሰረት አወንታዊና ምቹ የትምህርት ቤት ድባብ ከማዳበር አንጻር ወጥነት ያለው አሠራር መዘርጋት።

F. ግምገማ እና ሪፖርት

1. ቦርዱ የማህበራዊ-ስሜታዊ እና የአእምሮ ጤና ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ለአንደኛ ደረጃ፣ ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተዘጋጁ አማራጭ ፕሮግራሞችን እና የማህበራዊ-ስሜታዊ ደህንነትን እና የአእምሮ ጤና ፕሮግሮሞችን አገልግሎቶች ፍትሃዊ እና ውጤታማ የሰው ሃይል አቅርቦትን በመደበኛነት ይገመግማል።

2. የዚህን ፖሊሲ ግቦች ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስፈልጉ ስትራቴጂያዊ አተገባበሮች ውጤታማ ለመሆን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የበጀትና ገንዘብ ድጋፍ፣እና መሰል ባለሙያዎችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መመደብና ማሰማራት አለባቸው።

3. ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የግምገማ መርህ መሰረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

**ተዛማጅ ምንጮች:** MD Educ Code § 7-1501 (2018); Code of Maryland Regulations, sections 13a.07.11.03; 13a.05.05.02; 13a.12.03.02; 13a.12.03.07; 13a.12.03.11; 13a.12.03.08.08; 13a.12.04.08.08

**የፖሊሲው ታሪክ:** የቀድሞው ፖሊሲ IJA፣ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ (2004) የፀደቀው በ. , ውሳኔ ቁጥር ነው

~~A.—ዓላማ~~

~~የትምህርት ቦርድ ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በፍትሃዊነት ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች ሁሉን አቀፍ፣ ለተማሪዎች ዕድሜ የሚመጥን፣ግላዊ እድገትን እና አካዴሚያዊ ስኬትን ያገናዘበ አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።~~

~~B.—ጥናቶ~~

~~ሁሉን አቀፍ፣ ለተማሪዎች እድሜ የሚመጥን፣ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በትምህርት ቤት ካውንስለሮች የሚሰጡ አገልግሎቶች MCPS ለሁሉም ተማሪዎች የላቀ የአካዳሚክ ስኬት ተልእኮን ለማሳካት አስፈላጊ ናቸው።የትምህርት ቤት ካውንስለሮች ከፍተኛ ጥራት ላለው ትምህርት አሰጣጥ ወሳኝ አጋሮች በመሆናቸው የመማር ማነቆዎችን ለማስወገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመተባበር የትምህርት ቤት ካውንስለሮች በጠንካራ የትምህርት መርሃ ግብር ላይ ለስኬት አስፈላጊ የሆኑትን እውቀትና ክህሎት ያስተምራሉ እንዲሁም ከትምህርታዊ ስኬት ጋር በተያያዘ ጤናማ ማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገትን ያበረታታሉ። ካውንስለሮች የተማሪዎችን ስኬት ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማሰባሰብ ከሰራተኞች፣ ከወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት ጋር ይተባበራሉ። ካውንስለሮች ተማሪዎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው አካዴሚያዊ እና ግላዊ ዝንባሌአቸውን እንዲያሳኩ ይደግፏቸዋል።~~

~~C.—አቋም~~

~~1.—በሁሉም ትምህርት ቤቶች፡-~~

a) ~~ካውንስለሮች ሁሉን አቀፍ፣ ለዕድገት ተስማሚ የሆነ የትምህርት ቤት የማማከር አገልግሎት ለሁሉም ተማሪዎች ይሰጣሉ~~

b) ~~የትምህርት ቤት የማማከር አገልግሎት መርሃ ግብር ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ ተልዕኮ ጋር ይጣጣማል~~

c) ~~ካውንስለሮች ስለ አካዳሚክ ፕሮግራሞች፣ የማህበረሰብ ድጋፎች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች መረጃ እና ድጋፍ ይሰጣሉ~~

d) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች ሀሳብን በትክክል ለመግለጽ ሂደት እና የተማሪን ቀጣይ ስኬት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት አስፈላጊ ናቸው~~

e) ~~የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ መርሃ ግብር በብሔራዊ ደረጃ የተመሰረተ ሲሆን የመከላከል፣ ጣልቃ ገብነት እና ችግር ሲያጋጥም ምላሽ የመስጠት አገልግሎቶችን ያካትታል~~

f) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች ግላዊ፣ በሰዎች መካከል፣ የጤና፣ የአካዳሚክ እና የሙያ ማጎልበትን ለሁሉም ተማሪዎች በክፍል ፕሮግራሞች እና በሌሎች አገልግሎቶች አማካኝነት ያስተዋውቃሉ~~

g) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች ለባህል ተስማሚ በሆኑ ጣልቃገብነቶች የግለሰብ ተማሪዎችን ልዩ ፍላጎቶች ያሟላሉ።~~

h) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች የትምህርት ቤቱን የካውንስሊንግ መርሃ ግብር ሚና እና ግቦች ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሰራተኞች፣ አስተዳዳሪዎች እና ማህበረሰብ ጋር ይነጋገራሉ~~

i) ~~የትምህርት ቤት የማማከር መርሃ ግብር እና የት/ቤት ካውንስለሮች የተለያየ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ፍላጎቶችን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ያሟላሉ፤ እና ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ልቀት ያስተጋባሉ።~~

j) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች የተማሪ ፍላጎቶችን ለመለየት እና መፍትሔ ለመሻት እና የማማከር ፕሮግራሙን ለማዳበር፣ ለመተግበር፣ ለመገምገም እና በቀጣይነት ለማሻሻል የጥራት እና ብዛት መጠን መረጃዎችን በመሰብሰብ ይገመግማሉ።~~

2. ~~የትምህርት ቤት የማማከር አገልግሎት መርሃ ግብር ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍሎች ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል። የተማሪዎች አካዴሚያዊ እና የዕድገት ፍላጎቶች እያደጉ በሚሄዱበት ወቅት ስለሚለዋወጡ፣ የማማከር ፕሮግራሙ ከሰራተኞች፣ ከወላጆች እና ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር በየትምህርት ቤቱ ያሉ የተማሪዎችን ልዩ የትምህርት እና የእድገት ፍላጎቶችን ይመለከታል/ለማወቅና ለመረዳት ጥረት ያደርጋል።~~

a. ~~በኤለመንተሪ ት/ቤት ደረጃ፡~~

(1) ~~የትምህርት ቤት የማማከር መርሃ ግብር ተማሪዎች ለአካዳሚክ ስኬት አስፈላጊ የሆኑትን ክህሎቶች እና ዝንባሌዎችን እንዲያዳብሩ በመርዳት በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ ያበረታታል።~~

(2) ~~የትምህርት ቤት የማማከር መርሃ ግብር ውሳኔ አሰጣጥን፣ ችግር መፍታትን እና ተግዳሮትን የመቋቋም ችሎታዎችን ያስተምራል።~~

(3) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች አወንታዊ የራስን ፅንሰ-ሀሳብ እና የሌሎች ግለሰቦችን ችሎታዎች በማቀናጀትና በማስተባበር ያዳብራሉ።~~

b. ~~በመካከለኛ ትምህርት ቤት ደረጃ፡~~

(1) ~~የትምህርት ቤት የማማከር አገልግሎት መርሃ ግብር የአካዳሚክ እና ማህበራዊ ብቃት እና የሙያ ግንዛቤን በመገንባትና በማሳደግ ላይ ያተኩራል።~~

(2) ~~የት/ቤት ካውንስለሮች ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቂያ መስፈርቶችን የሚያሟላ እና ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የድህረ ምረቃ ግብ አቅድን የሚያንፀባርቅ ጠንካራ፣ ተገቢ አጠቃላይ እቅድ የሚያዘጋጁበትን ሂደት ያስተባብራሉ፣ ይቆጣጠራሉ እና ይመራሉ~~

c. ~~በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡~~

(1) ~~የትምህርት ቤት ካውንስለሮች በአካዳሚክ እና በሙያ ስራ አቅድ ሂደት ውስጥ ለመገምገም፣ ለመምራት እና ለመርዳት ከተማሪዎች ጋር በመደበኛነት ይገናኛሉ። የትምህርት ቤት ካውንስለሮች የተማሪዎችን የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታዊ እና የስራ አቅድ ግቦችን ለመደገፍ አጠቃላይ አቅዶችን ለመገምገም እና ለማሻሻል የተማሪዎችን አሠራር ሂደት ያቅዳሉ እና በአግባቡ እንዲከናወን ይመራሉ~~

(2) ~~የትምህርት ቤት የማማከር ፕሮግራም ተማሪዎችን በውሳኔ አሰጣጥ፣በሙያ አቅድ ማውጣት፣ በማህበራዊ ግንኙነቶች፣በግል ሃላፊነት እና ሌሎች ውጤታማ ዜጋ ለመሆን አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ያስታጥቃቸዋል።~~

## ~~D.—ተፈላጊ ውጤቶች~~

~~በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም ተማሪዎች አካዳሚያዊ ስኬትን እና ለግላዊ አደገታቸው የሚመጥን ሁሉን አቀፍ፣ ተስማሚ የሆኑ የት/ቤት የማማከር ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ያገኛሉ/ተደራሽነት ይኖራቸዋል። በሁሉም ትምህርት ቤቶች ደረጃ፣ የት/ቤት ካውንስለሮች ከወላጆች፣ ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች እና ከማህበረሰቦች ጋር በመተባበር የመማር እንቅፋቶችን ለማስወገድ እና ተማሪዎች ሙሉ አቅማቸውን በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ እና አካዳሚያዊ እና ግላዊ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሳኩ ለማስቻል እድሎችን እና ድጋፎችን ይሰጣሉ።~~